ከቃሊቲ የመጣ ደብዳቤ

ሰላም ላንተ ይሁን። እኛ ደህና ነን። ምንም እንኳዋን አካላችን ከዕለት ወደ ዕለት ቢዝልም መንፈሳችን እጅግ ጠንካራ ነው። ለብዙ ግዜ ደብዳቤህን ጠብቄ በማጣቴ የተሰማኝን ቅሬታ ልደብቅህ አልፈልግም። ምን ያህል ደብዳቤዎችህ በተለይ መረጃ ያዘሉት መንፈሴን እንደሚያጠነክሩትና እንደሚያድሱት ብታውቅ አትሰንፍም ነበር። ለማንኛውም ወደፊት በሰፊው እጠብቃለሁ። የፃፍከውን ደብዳቤ አይቼ በምታደርጋቸው ጥረቶች በጣም ደስ ብሎኛል። ሥራውም እስኪጀመር ኝጉቻለሁ። በጣምም አመሰግናለሁ።

ከቅንጅት መሪዎች ጋር በጣም የሚያስደስት ግንኙነት ነው ያለኝ። አንተ ከምታውቃቸውም ከማታውቃቸውም ጋር ግንኙነቴ አስደሳች ነው። በተለይ ከዶክተር ብርሃኑ ጋር ያለኝ ግንኙነት የሚያስደስት ነው። ዶክተር በፈቃዱ፣ ዶክተር ያዕቆብ ኢንጅኔር ሃይሉ ሻውልና ሌሎችም ብዙዎች በጥሩ ዓይንና ተስፋ ስለሚመለከቱኝ ለራሴ ያለኝ አመለካከት ሳይቀር ፍፁም የተቀየረ ነው። አንድ በጣም መረዳት ያለብህ ነገር አለ። ይኸውም አውሮጳ የሚሸተው ተስፋና እዚህ በአገር ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በጣም የተለየ ነው። በዚህ አገር ላይ ወያኔን ከሥልጣን አውርዶ በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመፍጠር ገና ረጅም ጉዞ የሚያስኬድ ይመስላል። በጠየቅከው መሠረት የቅንጅትን የወደፊት ሃሳብ ልነግርህ እችላለሁ። ግን የእኛን በጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት ውስጥ የመፈታት ነገር ፈፅሞ አታስበው። ወያኔ ገና ከልቡ አልተንበረከከም። ገና ነገሮች አስጨንቀው አልያዙትም። በእርግጥ አሁን አደገኛ በሆነ መልኩ ችግር ውስጥ እየገባ ነው። በተለይ በሱማልያ በኩልና በኢኮኖሚ ውድቀት፣ ቢሆንም ገና ብዙ የመውጫ ዕድል እንዳለው ያስባል።

በቅርቡ ሰዎች ለማደራደር ወደኛ መጥተው ነበር። ዋናው መሪ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሥሐቅ ነው። ቀናነት የሞላቸው ሰው ቢሆኑም ገና ነገሮች ጥርት ብለው የሚታያቸው አይደሉም። ከኢሕአዴግ በኩል ከልብ ለመደራደር ሳይሆን የኛን ቴምፕሬቸር ለመለካት ዓይነት ነው። ቀልደኛ የሆኑ ሃሳቦችን ይልካሉ። በግልፅ ባያወጡትም በተወሰኑ ቃላት የሚላከው መንግሥትን በነገር ሁሉ እንድንደግፍ፣ በተለይ ሽብርተኝነትን መዋጋት ተብሎ ሶማሌ ላይ ለተከፈተው ጦርነት ከጎኑ እንድንቆም፣ ሕገመንግሥቱን የማይቀበሉ የሚልዋቸውን እንድናወግዝ፣ ላያንሱንም እንድናወግዝ--- ይህን የመሳሰሉ ዕድሜውን በሥልጣን ላይ የሚያረዝምለትን ነገሮች ይፈልጋል። በምትኩ መፈታትን እንደስጦታ ሊሰጠን ይፈልጋል። በእኛ ዘንድ ጥሩ አቋም ነው ያለው። በመጀመሪያ ደረጃ ማንም ለመፈታት የማይኝኝ የለም። ነገር ግን መንግሥት መጀመሪያ ከእኛ ጋር መደራደር ከፈለገ፣ እኛ የሕሊና እሥረኞች ነን። መጀመሪያ ነፃ መውጣት አለብን። ነፃ ሳንሆን ድርድር የለም። ሁለተኛ ሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች መፈታት አለባቸው። ጋዜጠኞች፣ ሲቪል ማሕበራት መሪዎች መፈታት አለባቸው። ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲ ቢሮዎች መከፈት አለባቸው። ነፃ ጋዜጦች ተግባራቸውን ማከናወን አለባቸው። ያገሪቱን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ችግርን መፍታት ይገባናል የሚሉ ሃይሎች የሚሳተፉበት ጉባዔ በአጭር ግዜ ውስጥ መሠራት አለበት። እነዚህንና የመሳሰሉትን መነሻ ሃሳቦች ተግባራዊነት የሚያረጋግጥ ነፃ አካል መሠየም ያስፈልጋል፡ የሚሉና ይህን የመሳሰሉ ጠንካራ አቋሞች ነው ያሉት። ስለዚህ አትስጋ።

በእርግጥ ባለው የክስ ሂደት ለየካቲት 12 ለብይን ተቀጥረናል። ምንም ዓይነት ማስረጃና ምሥክር ያልቀረበባቸው ይለቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል። አቃቤ ሕግ ከ365 ምሥክር 289 ያህሉን አላሰማም። ይበቃኛል ብሎ ምሥክር ማሰማቱን አቁሞአል። በእኔ እምነት በአሁኑ ክስ ነፃ ብወጣ እንኳዋን ከበር ጠብቀው መልሰው እንደሚያሥሩኝ አልጠራጠርም። እናም ሌላ አዲስ ፋይል ይከፍቱብኛል። ይህን ዓይነት አሠራር የፖለቲካ እሥረኞች ላይ ሲፈፅሙት ቆይተዋል። ለማንኛውም የወደፊቱን የሚያውቀው እግዜር ብቻ ነው። እናም ብዙ አልጨነቅም። እርግጠኛ ሆኜ የምነግርህ ነገር ሕይወቴ በመረጥኩት ጎዳና እየሄደ ነው። አልጭነቅም። ለመፈታትም ብዙ አልጓጓም። ለብዙ ሚልዮኖች ነፃነት፣ ለፍትሕና ብልፅግና (ዴሞክራሲ) ነፍሴ ብታልፍም ቅር አይለኝም። ለዚህም የተፈጠርኩ ይመስለኛል። እንደማንኛውም ዜጋ አንገቴን ደፍቼ ልጅ ማሳደግ፣ ሌላም ሌላም አላቃተኝም። ያ ሕይወት ሁሉም ሰው የሚኖረው ቀላሉ ሕይወት ነው። በሕይወቴ መጨረሻ በዚያ ሕይወት ውስጥ ያለፈውን እኔነቴን ለማየት ሳይሆን አሁን እያለፍኩ ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ያለውን እኔነቴን ለማየት ወድጄና ፈቅጄ ነው እየሄድኩበት ያለሁት። በርግጥ ከደህና ቤተሰብ ባለመፈጠሬ የምፈልገውን ነገር ሁሉ በነፃነት ማራመድ አልችል ይሆናል። ሁሌም ስለቤሰብ አስባለሁ። ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር በረዳችሁ መጠን እንደምትጠይቃቸው የሁሉንም ውለታ ለመመለስ እግዜር ያብቃኝ።

ያሠሩን ሰሞን የጥቅምትና የህዳር ወራት ውስጥ ከተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የቀበሌ ጽሕፈት ቤቶችና ከጊዜያዊ ማጎሪያ ቤቶች የተለያዩ መጥፎ “ምርመራዎች” ተደርገውብን ወደማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በጨለማ ከሰበሰቡን በህዋላ “ምርመራው” ሳይቆም፣ አንድ ሰው ከሌላ እሥረኛ ጋር ሳይገናኝ ከ20-30 ቀን ያህል ለየብቻ ታሥረን “ሲመረምሩን” ቆይተው በህዋላ በግሩፕ በግሩፕ አድርገው አሠሩን። ሁላችንም ላይ ከትንሽ እስከትልቁ ጉዳት የደረሰብን ሲሆን በተለይ ግን ኢንጅኔር ሃይሉ ሻውል ላይ የደረሰው ጠባሳው (ጉዳቱ) አልጠፋም። ውሃ በሚያመነጭና እጅግ በጣም ቀዝቃዛ በሆነ ክፍል ውስጥ ከ20 ቀን በላይ የተዘጋባቸው ሲሆን በዚያ ምክንያት እስካሁን ድረስ እግራቸውን በትክክል ማንቀሳቀስ አይችሉም። ያ ክፍል በቅጽል ስሙ ፍሪጅ ክፍል ይባላል።

ወደቃሊቲ ከወረድን በህዋላ በተለይ አሁን በዚህ ወቅት ስለአለንበት ሁኔታ በትንሹ ለመግለጽ የተለያዩ ዓይነት እሥረኞች ሲኖሩ በፖለቲካ ምክንያት፣ በነፍስ ግድያ፣ በዘረፋ፣ አደገኛ ቦዘኔ በሚል፣ በሙስና እና በሌሎች የታሠሩ ሲሆኑ ከ16 እስከ 70 ዓመት በላይ የሚሆኑ አዛውንቶች ይገኙበታል። ከዚህም መሃል የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው፣ የዕድሜ ልክና ከ10 ዓመት በላይ ፍርደኛ የሚሆኑም በርካቶች አሉበት። ከዚህ በተጨማሪ ከ10 ዕመት በታች የተፈረደባቸውና የቀጠሮ እሥረኞችም ይገኛሉ። ብዙዎቹ ከእኛ ውጭ ያሉ የፖለቲካ እሥረኞች የኦነግ አባላት በሚል የታሠሩ ሲሆኑ ከምርጫ 97 በህዋላና ከስድስት ዓመት በላይም ፍርድ ሳያገኙ የታሠሩ ይገኙበታል።

አንዱ ክፍል አደገኛ ሌቦች በመባል ከታሠሩት ውስጥ የተወሰኑ ሰዎች እጃቸው በሰንሰለት ወይም በካቴና የታሠሩ ሲሆን እጅግ አደገኛ በሚል እጅና እግሩም ጭምር በሰንሰለት የታሠረ ይገኛል። በአጠቃላይ እዚህ ቦታ ውስጥ ሲያል ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ የከፋው ዞን ግን በተለይ ሙሉነህ ኢዩኤል፣ አንዱዓለም አራጌ ከቅንጅት ሲሳይ አጌና እና እስክንድር ነጋ ከጋዜጠኞች የነበሩበት ግቢ ውስጥ ከ3200 (ከሦስት ሺህ ሁለት መቶ) በላይ ሰው ሲኖርበት እነአቶ ክፍሌ ጥግነህ ከሌሎች 125 በላይ የሚሆኑ የቅንጅት እሥረኞች ጋር 1600 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ሰው በላይ ይገኝበታል።

በመቶዎች የሚቆጠሩ እሥረኞች በአንድ ክፍል ውስጥ ሲኖሩ ከ 50 በላይ ተደራራቢ አልጋዎች፣ ከመቶ በላይ ሰዎች በጥግ ላይ አልጋ ይዘው ሲተኙ በመሃሉ ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መሬት ላይ ተጠጋግተው ይተኛሉ። በተለያየ ግዜ ይህ ቁጥር ይጨምራል ወይም ይቀንሳል። መሬት ከሚተኛው ሰው የተወሰኑት፣ ሰው ሲበዛ በአንድ ፍራሽ ለሁለት ይተኛሉ። የቤቱ ስፋት ሲሰላ ከጥቂት መቶ ካሬ ሜትር የማይበልጥ ሲሆን ለአንድ ሰው በአማካኝ ከግማሽ ካሬ ሜትር ትንሽ ከፍ ያለ ቦታ ይደርሰዋል ማለት ነው። ከዚህች ቦታ ነው የሚያድረው፡ የሚውለው፣ ምግብ የሚበላው ማለት ነው። በተለይ ራት በሚበላበት ግዜ በሩ ከተዘጋ በህዋላ ስለሆነ መፈጠርን ያስጠላል። ማረሚያ ቤቱ የምግብ መመገቢያ ሰሃን ስለማይሰጣቸው ምግባቸውን የተወሰኑት ላስቲክ አንጥፈው የሚበሉ አሉ። እኛ ተራ ገብተን ከቤት ምግባችንን እያስመጣን የምንመገብ ሲሆን ከማረሚያ ቤቱ የሚቀርበውን ምግብ አንጠቀምም። ማረምያ ቤቱ ጥቁር የሆነና እንቅጥቅጥ (ቁሻሻ አፈር ) የተሞላ እንጀራ ከሽሮ ጋር ይሰጣል። ምግቡ በጣም ጣዕም የሌለው ከመሆኑ የተነሳ ብዙም የሚበላው ሰው ስለሌለ አንድ ሰው መመገብ ከፈለገ እችላለሁ የሚለውን ያህል መጠን መውሰድ ይችላል። ከዚህ በተለየ መልኩ ግን ጠዋት ለቁርስ የሚሰጠን ዳቦ በጣም ጥሩ ሲሆን ማንኛውም ሰው ተቀብሎ የሚመገበው ነው። ሻዩ ግን አይመረርምም፣ አይጣፍጥምም። እሱን የፈለገ በብርጭቆ የፈለገ በጃግ መውሰድ ይችላል።

የጤና አጠባበቅን በሚመለከት ሁሉን መግለጽ ይከብዳል። ሁሉን ብንነግራችሁ ማጋነን ነው ብላችሁ ስለማትቀበሉት የተወሰነውን ብቻ ልንገራችሁ። በእሥር ቤቱ ውስጥ ያሉትን የአእምሮ ሕመምተኞች እያባበልንና የተሻለ ምግብ እየሰጠን በጥንቃቄ እንጠብቃቸዋለን። ጥቂት ደግሞ ዓይነ ሥውራን ሲኖሩ በ HIV መያዛቸውን በግልፅ ያወቁ በርከት ያሉ ሰዎች አሉ። ዕድሜያቸው የገፋና ሲስሉ የሚያድሩ የሳንባ በሽተኞችም በተጨማሪ ይገኛሉ። ጉንፋንና የቆዳ በሽታ በብዙ ቁጥር ከመኖራቸው የተነሳ እንደኮመን ነገር ነው የሚታዩት። በአንድ ቀን ወደ ክሊኒክ እንዲወጣ ያለው ኮታ አምስት ያህል ሰው ብቻ ሲሆን በብዙ ጭቅጭቅ ሰባት ሆንዋል። ይህንን ዕድል የሚያገኘው በጣም የባሰበት ሕመምተኛ ነው። በሩ ከጠዋቱ 12 ስዓት እስከ ቀኑ 11 ሰዓት እደጅ እንድንወጣ ክፍት ነው።

በአጠቃላይ ቃሊቲ እውነተኛ የገሃነም ደጃፍ ነው ማለት ይቻላል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ለነገሮች የነበረኝ አመለካከት ቀለል ያለ ነበር። አሁን ግን ፍጹም ተለውጦዋል። የወደፊት ሕይወቴን ዓላማ ከዚህ እሥር ቤት ሆኜ ግልፅ አርጎ ማስቀመጥ በጣም ይከብዳል፣ ምክንያቱም ነገሮች በፍጥነት የሚለዋወጡበት ቦታ ቢኖር እሥር ቤት ነው። በነገሮች መለዋወጥ አእምሮዬ እንዳይጎዳ ራሴን ለመጠበቅና ወደፊት የሚመጣውን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ። ከሚደርስብኝ ዛቻ፣ ስድብና ማስፈራራት

አንፃር በተለይ እንደኔ ዓይነቶችን የፖለቲካ እሥረኞችን በየግዜው ነገር ይፈልጉናል። ይህን ዓይነት ነገር የሚያደርጉት አውጥተውም ለመረሸን ሁሉ እንደሆነ ይጠበቃል።

በእኔ በኩል ግን ምንም እንክዋን የመጨረሻው ግዜ ግልፅና ጥርት ባለ መልኩ የተቀመጠ ቢሆንም እንደየወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አካሄድ ሊለያይ ይችላል። እስከ መጨረሻው ግን የፍቅር ሰው መሆን እሻለሁ። እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምችለው ይህንን ሁሉ ክፉ የሚያደርጉብኝን ሰዎች ከሰሙትና ካወቁት እውቀት አንፃር ነው እንጅ ከፍጥረታቸው ክፉ ሰዎች ወይም ክፉ ዘሮች ሆነው አይደለም። ሕይወትንንና አገርን ከእኛ አንፃር እስኪያዩትና ነፃነትና ዴሞክራሲ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሳይቀር ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ እንዲረዱት ማድረግ እንዳለብን ይሰማኛል። ይህ የሚሆነው በፍቅርና በፍቅር ብቻ ነው። ወደፊት በዚህ አገር እውነተኛ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሠረተ የመንግሥት አወቃቀርን እስኪመሠርቱ ድረስ በሰላማዊ መንገድ ከመታገል ወደሁዋላ የማልል ሰው ስሆን ፓርቲዬ በብዙ ኢትዮጵያውያን ግፊት የተፈጠረና በመቶዎች የሚቆጠሩ ደማቸውን አፍስሰው ሞተውለታል፣ ቆስለውለታል። በሺዎች የሚቆጠሩ ዛሬም ድረስ በተለያዩ የአገሪቱ ማጎሪያ እሥር ቤቶች ይገኛሉ። ይህ ሁሉ በዚህ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር የተቆራኘ ነው። ይህን ለማሳካት በሕይወት መኖርና ይበልጥ እውቀትን ማጎልበት አለብኝ። አሁን በእሥር ቤት ላይ ጥሩ ለማንበብና ሰዎች ከረጅም የሕይወት ልምዳቸው ያፈለቁትን እውቀት ለመካፈል ችያለሁ። ለወደፊቱ formal በሆነ መልኩ ትምህርቴን መቀጠል እፈልጋለሁ። ግን ትምህርቱ ከፖለቲካው መስመር የማያወጣኝ ትምህርት ነው የምፈልገው። በዚህ ፓርቲ ውስጥ ሊያሠራኝ በሚችል መልኩ ጥሩ እውቀት እሻለሁ። የፍትሕ የበላይነትና ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እስኪፈጠር ድረስ መታገሌን እቀጥላለሁ። ከሁሉ በላይ የሚያሳስበኝ የወያኔ መውደቅ ብቻ ሳይሆን እሱ ሲወድቅ የሚፈጠረው ሥርዓት መልሶ ሰዎችን በከባድ አፈናና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳይከት ነው። ስለዚህም የቻልኩትን ከማድረግ ወደህዋላ አልልም።

የፓርቲውን የወደፊት ዓላማ በዝርዝር ለመግለጽ እኔ ማንዴቱ የለኝም። እናም እኔ የምሰጠው ቃል እንደመጨረሻ የፓርቲው ቃልና ሃሳብ መወሰድ የለበትም። በዚህ ከተስማማን ጠቅለል ያለ የፓርቲውን የወደፊት ዓላማ ለማስቀመጥ ያህል መጀመርያ መታወቅ ያለበት ፓርቲው እጅግ ዴሞክራሲያዊ ከመሆኑ በውስጥ በተለይ አመርራር ላይ ያሉት ሰዎች በየግላቸው ለዴሞክራሲ ያላቸው ትንቢትና ዓላማ በጣም የሚያስገርም ነው። ስለሆነም ለፓርቲው አመራሮች ሆነ ለሌሎች፣ ከእሥር መፈታት በጣም አንገብጋቢ አይደለም። ምንም እንክዋን ያለንበት ቦታ ላይ አንድ ቀን ማደር ቢከብደንም፣ መፈታት ግን የመጀመርያው ዓላማችን አይደለም። የፓርቲው ዋና ዓላማ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ ተገንብቶ ማየት ሲሆን ከሁሉ በላይ አሁን ደግሞ ማንኛችንም አገራችንን ልናድናት የማንችልበት ደረጃ ላይ እንዳንደርስ እንሰጋለን። ስለዚህ ፓርቲው ሁልግዜ መርህ አድርጎ የሚጠይቀው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን ለማድረግ እንዲቻል በዚህች አገር ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ሁሉ በጦርነት ያሉትን ጨምሮ በጠረጴዛ ዙርያ ተሰብስቦ በመነጋገር በአጠቃላይ በአገሪቱ ብሔራዊ እርቅን ፈጥሮ አዲሲቱን ኢትዮጵያን በሁሉም እኩልነት ላይ የግለሰብን ነፃነት ባከበረ መልኩ መመሥረት ሲሆን በተመሠረተችው አገር ውስጥ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከዚህ በህዋላ የመንግሥት

ሥልጣን በተገደበና ተጠያቂነት ባለው መልኩ በምርጫ ብቻ የሚያዝዝበት አገር እንድትሆን ማድረግ ነው። ሌላው መታወቅ ያለበት ዓላማችን ኢ.ሐዴግን ማጥፋት አለመሆኑና እንዲያውም ራሱ ኢ.ሕአዴግ የዚህች አገር ችግሮች አንዱ የመፍትሔ አካል እንደሆነ ነው።

በዚህ ፓርቲ ውስጥ እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያለ ሰው አለ ብሎ ለማለት ይከብደኛል። በሕይወቱ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚሰጠው ቦታ የሰዎችን ነፃነት ለማየት ያለው ፍላጎት፣ እንደጠላት የሚያዩትን ሰዎች የሚወድድበት የፍቅር መጠን ሁሉ ለመግለፅ ይከብዳል። በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ብዙ ፍቅርን እንዳወጣ የረዳኝ ሰው በመሆኑ ከልቤ የማደንቀውና እንደሞዴል የምከተለው ሰው ነው። የወደፊቱ የዚህች አገር ተስፋ እንደሆነ ማንኛችንም ለሰከንድ  ያህል አንጠራጠርም። እንክዋን እኛ ያሠሩንም አካላት እጅግ በጣም ተረድተውታል። በእኔ በኩል ሁሉም አብረውኝ ቃላቸውን ጠብቀው የታሠሩትን ስዎች የማደንቅ ቢሆንም በተለይ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግን የሰዎችን ነፃነትና ዴሞክራሲ ለማየትና ነፃ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያለው ምኞትና ረሃብ ያንንም ተከትሎ የሚመጣውን የኢኮኖሚ እድገትና የሰላም ዋስትና ለሁሉም ዜጎች ለማምጣት ያለውን ቅንአት ሳይ በእርግጥ አይደለም ኑሮና፣ እሥሬንም ሞቴንም ከሱ ጋር ቢያደርገው ቅር አይለኝም። ይህች አገር ይህንን ሰው መጠቀም አለባት። ፈፅሞ ልታጣው አይገባም። እውነተኛ ሶሻል ዴሞክራት ነው። እኔም አድናቂው ብቻ ሳልሆን ከእግሩ ስር እየተከተልኩ ፈለጉን እስከመጨረሻው እከተለዋለሁ።

በል እንግዲህ ከዚህ በላይ ያለውን ፅፌልሃለሁ። ምን ያህል እንደምትፈልገው ባይገባኝም በተቻለ መጠን ፅፌልሃለሁ። አንተም የደረስክበትን ፃፍልኝ። ወደፊት እፅፍልሃለሁ።

ያንተው ወዳጅ፣